# የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

## መመሪያ ቁጥር 191/2018

## የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ

# Addis Ababa City Environmental Protection Authority

## Directive No. 191/2026

## Construction Minerals Licensing Directive

ሰኔ፣ 2018 ዓ.ም

July, 2026 G.C

## መመሪያ ቁጥር ቁጥር 191/2018
## የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ

ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች በቀጥታ በግብአትነት እየዋለ የሚገኘውን በከተማዋ ክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በማጥናት የማዕድን ማምረት ፈቃድ መስጠትና ማስተዳደር በማስፈለጉ፤

ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም የከተማዋ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር በማምረት፣ በመረጃ አያያዝና አቀራረብ ያለውን ኃላፊነት ተጠያቂነት ሊያሳይ የሚችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## Directive No. 191/2026
## Construction Minerals Licensing Directive

Whereas, it has become necessary to conduct proper studies on the various construction minerals found within the city administration and used as direct inputs for different development activities, as well as to regulate the issuance and administration of mineral production licenses;

Whereas, it has become necessary to ensure the sustainable and efficient utilization of the city's limited natural resources in order to adequately meet the demand for construction minerals;

Whereas, it has become necessary to put in place an operational framework that ensures accountability among all relevant stakeholders in relation to service delivery, licensing procedures, and the monitoring, control, registration, and supply of mineral deposits;

Now, therefore, pursuant to the powers and duties vested in it under Article 16(2)(e) of Proclamation No. 84/2016, issued for the reestablishment of the Executive and Municipal Service Organs of the Addis Ababa City Administration, the Addis Ababa City Administration Environmental Protection Authority hereby issues this Directive.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 191/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 ከነማሻሻያው ነው፤
2. **"ደንብ"** ማለት የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 423/2010 ነው፤
3. **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው፤
4. **"ውል"** ማለት ባለሥልጣኑና በባለፍቃዱ መካከል የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረትና የማምረቻ ማሽን መትከያ ፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ስምምነት ነው፤
5. **"ክምችት"** ማለት በከርሰ ምድር ውስጥ በአንድ በተወሰነ ስፍራ በተፈጥሮ የሚገኝ የኮንስትራክሽን ማዕድናትና ማዕድን ነው፤
6. **"አምርቶ የመሸጥ ፈቃድ"** ማለት ማዕድኑን አምርቶ ለገበያ ማዋል ነው፤
7. **"አምርቶ የመጠቀም ፈቃድ"** ማለት ምርቱን አምርቶ ለራስ ወይም ለመንግስት ልማት ማዋል ነው፤
8. **"የምርት ማንሻ ፈቃድ"** ማለት ፈቃዱ በተለያየ ምክንያት ሲሰረዝ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ተመርቶ የተከማቸ ምርት ሲኖር እንደምርቱ መጠን በጊዜያዊነት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

## Section One
## General Provisions

1. **Short Title**

This directive may be cited as the "Construction Minerals Licensing Directive No. 191/2026."

2. **Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this directive:

1. **"Proclamation"** means the Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended).
2. **"Regulation"** means the Mining Operations Council of Ministers Regulation No. 423/2010.
3. **"Authority"** means the Environmental Protection Authority of the Addis Ababa City Administration;
4. **"Contract"** means an agreement made between the Authority and a licensee in relation to a construction mineral production and processing plant installation license;
5. **"Deposit"** means construction minerals and mines found naturally in a specific area within the earth's crust;
6. **"Producing and Selling License"** means to extract and bring minerals to the market;
7. **"License to produce and use"** means to use the product for personal use or for government development;
8. "**License issued for lifting the product"** refers to a license issued

9. ‹‹**አልሚ**›› ማለት የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤
10. "**የሥራ ፕሮግራም**" ማለት ማዕድን ለማምረት የሚቀርብ የስራ ዝርዝር ሲሆን፡ ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ፡ ወጭውን መዋቅሩን የሚያመላክት እቅድ ነው፤
11. "**የፈቃድ ስም ለውጥ**" ማለት ቀደም ሲል በተሰጠው የማዕድን ማምረት ፈቃድ መሰረት ምንም አይነት የባለቤትነት ለውጥ ሳይኖር ወይም ባለቤትነትን ሳያሳጣ የፍቃዱ ስም ለውጥ ብቻ ሲደረግ ነው፤
12. "**የማምረቻ ማሽን መትከያ**" ማለት ለማዕድን ማምረቻነት በቀጥታ የሚያገለግሉ የድንጋይ መፍጫ ማሽንን እና ባቿንግ ፕላንት ለመትከል፤ ሎደር ዶዝር እና የመሳሰሉትን ማሽነሪዎችን ማስቀመጫና የምርት ማከማቻ ቦታ ነው፤
13. "**ባለፈቃድ**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤
14. በአዋጁና ደንቡ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ ሲውሉ በአዋጁና ደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤
15. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለማምረት ፈቃድ በተሰጣቸው ወይም በሚሰጣቸው ግለሰቦች፤ ማህበራት፤የግልና የመንግስት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

temporarily when there is a product produced for special reasons and stored, based on the production amount or when the license is canceled;

9. "**Licensee**" means an individual, organization, or association that has been given a license to produce construction minerals;
10. "**Work program**" means a detailed work plan submitted for the production of minerals, which indicates the time the work is carried out, the cost structure, and the plan;
11. "**Change of license name**" means when there is no change in ownership or the ownership is not transferred, and only a name change is made based on the previously issued mineral production license;
12. "**Processing plant installation**" means a place for installing stone crushing machines and granulators that directly serve the production of minerals, and a place for storing machinery and products such as loaders and excavators;
13. "**License holder**" means any natural or legal person;
14. Words and phrases defined in the Proclamation and Regulation shall have the same meaning when used in this manual;
15. What is expressed in the masculine gender in this manual includes the feminine.

4. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና የማይታደስ ሃብት ስለሆነ ሃብቱን ለመጠበቅ እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ለማሳደግ፣
2. የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ተገልጋዮችን ሊያረካ በሚችል መልኩ ቀልጣፋ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው ለማድረግ፣
3. የከተማውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ክምችት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ ጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃ ለማደራጀትና ተገልጋዮች መረጃውን ብቃት ባለው መንገድ እንዲጠቀሙና የአመራረት ሥራውን ዘመናዊ ለማድረግ፣
4. አካባቢን ያገናዘበና ከስነምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው እና ለከተማው ሁለንተናዊ ልማት የሚውል የኮንስትራክሽን ማዕድን ግብአት ማረጋገጥ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የማዕድን ፈቃድ</u>

5. <u>ስለማዕድን ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ሰው የኮንስትራክሽን ማዕድን ምርት ለማምረት ከባለስልጣኑ ፍቃድ ማግኘት አለበት፤
2. ማንኛውም ሰው ለመንግስት ልማትና ለህዝብ አገልግሎት ለንግድ ላልሆነ አላማ ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማእድን ማምረትና መጠቀም ይችላል፤

6. ህጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ለግንባታ ብቻ

3. <u>Scope of Application</u>

This Directive shall apply to any individual, association, private entity, or government institution that has been issued, or may hereafter be issued, a license to produce construction minerals within the jurisdiction of the Addis Ababa City Administration.

4. <u>Objectives of the Directive</u>

1. Since natural resources are owned jointly by the State and the people and are non-renewable in nature, the objective of this Directive is to ensure the protection of such resources and to maximize their economic and social benefits.
2. To establish a service delivery system that is efficient, transparent, and accountable, and that ensures customer satisfaction.
3. To organize and manage information relating to the city's construction mineral deposits through modern technology and proper studies, thereby enabling users to effectively utilize such information and promote modernization of production activities.
4. To ensure the sustainable supply of construction minerals in a manner that is environmentally sound and supportive of the city's overall development.

## <u>PART TWO</u>
## <u>MINERAL LICENSES</u>

5. <u>Concerning Mineral Licenses</u>

1. Any person must obtain a license from the Authority to produce construction mineral products.
2. Any person may produce and use

በግል ይዞታው ውስጥ ያለክፍያና ፍቃድ ሳያስፈልገው አምርቶ መጠቀም ይችላል፤

7. <u>**ፈቃድ የማይሰጥባቸው ቦታዎች**</u>

ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ወይም ስለቦታው የሚመለከተው ህጋዊ አካል ወይም ባለቤት ካልፈቀደ በቀር፡-

1. ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ቦታዎች፤
2. የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ስፍራዎች፤
3. ለመሰረተ ልማት አውታሮች በተከለለበት ቦታዎች፤
4. ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም በብሔራዊ ፓርክ በተከለሉ ስፍራዎች፤
5. ከመኖሪያ መንደሮች፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ከመሰረተ-ልማት አውታሮች 500 ሜትር፣ ከኤሌክትሪክ ተሸካሚ 25 ሜትር ከወንዝ ዳርቻ 30 ሜትር ክልል ውሰጥ፤

ፈቃድ አይሰጥም፤

8. <u>**ፍቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**</u>

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡-

1. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተግባሩን ማካሄድ የሚችል
2. የማእድን ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን መረጃ ማሟላት የሚችል፤
3. ስለቦታው ከሚመለከተው አካላት የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም የውል ስምምነት የሚያቀርብ፡፡

construction minerals for non-commercial purposes for government development and public services with the authorization of the Authority.

**6.** Legal landholders may produce and use minerals, only for construction purposes, on his/her own private possession, for non-commercial purposes without payment and a license.

**7.** <u>**Areas Where Licenses are Not Granted**</u>

Unless authorized by the Authority under special circumstances or by the relevant legal body or owner of the site:

1. Areas reserved for cemeteries and religious matters;
2. Sites containing pre-historical heritages or those designated as national monuments;
3. In areas reserved for infrastructure networks;
4. In areas designated for environmental protection or within national parks;
5. No license shall be issued within a radius of 500 meters from residential villages, industrial parks, and infrastructure utilities; a radius of 25 meters from electric transmission lines; and a radius of 30 meters from riverbanks;

no license shall be issued.

**8.** <u>**Eligibility for Obtaining a License**</u>

Without prejudice to the provisions stipulated under the Proclamation, any

9. <u>ፈቃድ የሚሰጥባቸው የኮንስትራክሽን ማዕድን አይነቶች</u>
   1. ጥቁር ድንጋይ፣
   2. ገረጋንቲ፣
   3. ቀይአሸዋ፣
   4. ቀይአፈር፣
   5. ነጭ የግንብ ድንጋይ ወይም ጥርብ ድንጋይ/፣
   6. የወንዝ አሸዋ ወይም ጠጠር እና ሌሎች ተመሳሳይ ማዕድናት ናቸው፡፡

10.<u>የሚሰጡ የፈቃድ ዓይነቶች</u>
የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ፈቃድ ዓይነት፡-
ሀ) አምርቶ የመሸጥ ፈቃድ፤
ለ) ለመንግስት ልማት ስራዎች አምርቶ የመጠቀም ፈቃድ፤
ሐ) የምርት ማንሻ ፈቃድ፤
መ) ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መሳሪያ/ማሽን/ መትከያ ፈቃድ፤
ሠ) ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ፈቃዶች፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>ኃላፊነት እና ተግባር</u>

11. <u>የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>
በማዕድን ሥራዎች አዋጅ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016 የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-
   1. ለማዕድን ሥራዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በመቀበልና በመመርመር ውድቅ ማድረግ ወይም ማፅደቅ፤
   2. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚችል መሆኑን

person seeking to obtain a license shall fulfill the following requirements:
   1. Legally authorized to carry out the activity in accordance with the relevant laws;
   2. Capable of providing the required information for conducting mining operations;

3. Submit proof of ownership of the land or a contractual agreement from the relevant authorities concerning the site.

9. <u>**Types of Construction Minerals for Which Licenses May Be Issued**</u>
   1. Black stone;
   2. Gravel;
   3. Red sand;
   4. Red soil;
   5. White masonry stone or chipped stone;

6. River sand or gravel and other similar minerals

10. <u>**Types of Licenses Issued**</u>
Types of Construction Mineral Production Licenses:
a) Production and sale license;
b) Production and utilization license (for government development projects);
c) Production lifting license;
d) License for installation of equipment/machinery related to the operation;
e) Other licenses related to the operation.

ማረጋገጥ፤

3. የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት አዲስ ፈቃድ መስጠት፤ነባር ፈቃድ ማደስ እና ስም ማዛወር፤ ስም ለውጥ እና የማምረት ፈቃድ መሰረዝ፤
4. ከስራው ጋር በተያያዘ ለድንጋይ ወፍጮ መትከያና ተያያዥ ተግባሮች ፈቃድ መስጠት፤
5. በጥናት የተገኙትን የማዕድን መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማደራጀትና ማሰራጨት፤
6. የአዋጭነት ጥናት እና የተጽዕኖ ግምገማ ሰነዶችን መሠረት ያደረገ የማዕድን ማምርት ዘዴዎችን ፡ሙያዊ ምክር ይሰጣል እርምጃም ይወስዳል፤
7. በከተማዋ ክልል የሚገኙ የኮንስትራክሽን ማዕድን ቦታዎችን ያጠናል፤
8. በከተማዋ የተሰጡ ፈቃዶችን ይከታተላል ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል መረጃዎችን ያደራጃል፤
9. በክፍለ ከተማ ደረጃ በተሰጡ ውሳኔዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

12. <u>**የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት**</u>

1. በማእክል የተሰጡ ፈቃዶችን መከታተል፤መቆጣጠር እና መረጃ ማደራጀት፤
2. በማዕከል ለሚስጡ አዲስ እና ነባር ፈቃዶች ሙያዊ አስተያየት ይሰጣል፤
3. በህገ ወጥ መንገድ የሚመረቱ የማዕድን ቦታዎችን እና ያለደረሰኝ ሽያጭ የሚካሂዱትን

## PART THREE
## RESPONSIBILITIES AND DUTIES

**11.** <u>Powers and Responsibilities of the Authority</u>

Without prejudice to the powers and responsibilities provided under the Mining Operations Proclamation and the Addis Ababa City Administration Executive Bodies Establishment Proclamation No. 84/2016, the Authority shall:

1. Receive and examine applications submitted for mining operations and approve or reject them;
2. Verify that any license holder is capable of fulfilling the obligations specified in the license;
3. Issue new construction mineral production licenses; renew existing licenses; transfer ownership names; approve name changes; issue customs duty exemption approvals; and revoke production licenses;
4. Issue licenses related to stone crusher installations and related activities connected with the work;
5. Organize and disseminate mineral information obtained through studies using modern systems;
6. Provide professional advice and take measures regarding mining production methods based on feasibility studies and environmental impact assessment documents;
7. Conduct studies on construction mineral sites located within the city administration territory;
8. Monitor licenses issued within

ይከታተላል፣ቅጣት ይጥላል መረጃውን ለማዕከል ያሳውቃል፤

## ክፍል አራት

## ሌሎች የፈቃድ ድንጋጌዎች

**13.የማዕድን ፈቃድ የውል ዘመን**

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ፈቃድ ዘመን ፡-

1. ለጥቁር ድንጋይ ሥራ ፈቃድ ከፍተኛው አምስት አመት ሆኖ በየአመቱ የሚታደስ ይሆናል፤
2. ለገረጋንቲ፣ አሸዋ፣ ነጭ ድንጋይ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ከሁለት አመት ያልበለጠ ሆኖ በየአመቱ የሚታደስ ይሆናል፤
3. ለምርት ማንሻ ፈቃድ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል፤
4. ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መሳሪያ ወይም ማሽን መትከያ ፈቃድ ዘመን ከማዕድን ማምረቻ ፈቃድ የውል ዘመን ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የፈቃድ ዘመኑ ሲያበቃ ማንኛውንም ንብረት ነቅሎ መሬቱን ነጻ ማድረግ አለበት፡፡

**14.አዲስ የማዕድን ፈቃድ መስጠት**

የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ መረጃዎችን በማያያዝ አመልካች በፖርታል ማመልከት አለበት
2. የአመልካች ሙሉ ስም፡ፆታ፡ ዕድሜ፡ ዜግነቱን፡ የትውልድ ቦታውንና የያዘ ማመልከቻ እና የታደሰ መታወቂያ ማቅረብ፣
3. አመልካቹ የይዞታ ባለቤትንት መረጃ

the city, provide professional support, and organize relevant information;

9. Render decisions on complaints submitted against decisions made at sub-city level.

**12. Duties and Responsibilities of the Sub-City Office**

1. Follow up, supervise, and organize information relating to licenses issued by the central authority;
2. Provide professional opinions regarding new and existing licenses issued by the center;
3. Monitor illegally operated mining sites and sales transactions undertaken without an invoice, impose penalties, and report such information to the center.

## PART FOUR

## OTHER LICENSE PROVISION

**13. Duration of Mining Licenses**

Without prejudice to the provisions of the Proclamation, the duration of mining licenses shall be as follows:

1. A black stone mining license shall be valid for a maximum period of five years and shall be renewable annually;
2. Licenses for the production of construction minerals such as aggregate, sand, and white stone shall be valid for a period not exceeding two years and shall be renewable annually;
3. A product lifting license shall be issued for a period not exceeding

ከሚመለከተው የክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር እንዲሁም ይሁንታውን ለተጠየቀው አገልግሎት ማዋል ስለመቻሉ የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት የይሁንታ አስተያየት በደብዳቤ ማቅረብ አለበት፣

4. አልሚው የማልማት ፍቃድ የጠየቀው በመንግሰት ወይም በራሱ ይዞታ ላይ ካልሆነ ከህጋዊ ባለይዞታ ጋር በጊዜ ገደብ የተወሰነ እና በመመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠ ውል ማቅረብ ይገባዋል፤
5. ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ልዩ ልዩ የፈቃድ ክፍያ ማጠናቀቅ አለበት፤
6. ባለሥልጣኑ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው ሌሎች ህጋዊ መረጃዎች ሊያቀርብ ይገባል፤
7. አመልካች ድርጅት ከሆነ የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻና የወኪሉን ስምና አድራሻ መረጃ ይሰጣል፤
8. አመልካች ማህበር ወይም ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመሥረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ ያቀርባል፤
9. በህጋዊ አማካሪ የተጠና የአዋጭነት ጥናት እና ይሁንታ ያገኘ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሠነድ ማቅረብ ይገባዋል፣
10. በተፅዕኖ ግምገማው ጥናት መሰረት በአካባቢው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማስተካከል አስፈላጊ ነው የተባለውን የፋይናንስ ፍላጎት በመስሪያ ቤቱ ስም በተከፈተው

three months;

4. The duration of licenses for machinery or equipment installations related to the mining activity shall correspond to the duration of the mining production license, and upon expiry of the license period, all property shall be removed and the land cleared.

**14.** <u>Issuance of a New Mining License</u>

The following preconditions shall be fulfilled for obtaining a mining production license:

1. The applicant shall apply through the portal by attaching the required information to the Authority office;
2. The applicant shall submit an application containing their full name sex, age, nationality, and place of birth, together with a renewed identification card;
3. The applicant shall provide ownership information from the relevant sub-city land administration office, as well as a letter of approval from the Environmental Protection Office confirming that the requested activity is permissible for the intended service;
4. Where the developer seeks a development license on land that is not government-owned or personally owned, the developer shall submit a time-bound agreement verified by the relevant legal authority with the lawful landholder;
5. All applicable licensing fees shall be paid before the license is issued;

የባንክ አካውንት ዋስትና ገቢ ማድረግ አለበት፤

11. በየሶስት ወሩ ባለፈቃዱ አጠቃላይ የስራ አፈጻጸሙን እና በየወሩ የገቢ ሪፖርት በማቅረቢያ ቅጽ መሰረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

12. ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት እና ፈቃድ ከወሰደ በኋላ በየአመቱ የመልሶ ማልማት እቅድ ማቅረብ አለበት

15. <u>**በአርሶ አደርና በማህበር ለተደራጁ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

1. ስምና አድራሻ፣
2. ፈቃዱ የተጠየቀበት ማዕድን የሚገኝበት ሥፍራ፣
3. በቦታው የመጠቀም መብት ወይም ባለ ይዞታ ስለ መሆኑ ማረጋገጫ ከክፍለ ከተማው መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቅረብ አለበት
4. አርሶ አደሮቹ በኃ/የተ/የግ/ማ ወይም በሽርክና ወይም በሕብረት ሥራ ማሕበር ተደራጅተው መስራት ከፈለጉ በተገለጹት የንግድ አደረጃጀት ቅርጾች ስለመደራጀታቸው ህጋዊና ተገቢ ማስረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፤
5. በአርሶ አደር አደረጃጀትም ይሁን በሌላ የሽርክና አደረጃጀት ቅርጽ የተደራጁ አካላት ፍቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መንግስታዊ ግዴታዎችን እና ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፤

16. <u>**የፈቃድ መረጃ ምዝገባ**</u>

ፈቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱ አመልካቾች በሙሉ ፈቃድ የተሰጣቸው

6. The applicant shall provide any other lawful information requested by the Authority;
7. Where the applicant is an organization, it shall provide the address of its head office together with the name and address of its representative;
8. Where the applicant is an association or company, it shall submit copies of its memorandum of association and bylaws;
9. The applicant shall submit a feasibility study prepared by a legal consultant together with an approved environmental impact assessment document;
10. Based on the environmental impact assessment study, the applicant shall deposit the required financial guarantee into the bank account opened in the name of the office to address any potential environmental damage;
11. The license holder shall submit quarterly overall performance reports and monthly income reports in accordance with the prescribed reporting format;

12. Before obtaining the license and annually thereafter, the license holder shall submit a rehabilitation and restoration plan.

**15.** <u>Application submitted by Farmers and Associations for Mining Production Licenses</u>

1. Name and address;
2. The location where the mineral, for which the license is requested, is found;
3. Proof of land use rights or possession

እና የተከለከሉ አመልካቶች ዝርዝር ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዘመናዊ የመረጃ ስርአት መሰረት እንዲመዘገቡ ይደረጋል

17.<u>**የምርት ማንሻ ፈቃድ የሚሠጥባቸው ሁኔታዎችና ጊዜ ገደብ**</u>

1. ፈቃዱ ከሚያበቃበት ጊዜ በፊት በአስገዳጅ ሁኔታ ሲቋረጥ፣
2. ፈቃዱ ሲሰረዝ እና ያልተነሳ ምርት ካለ፣
3. በተለያዩ ግንባታዎች ምክንያት የተከማቸ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ሲኖር፣
4. የምርት ማንሻ ፈቃድ የሚሰጠው በባለሙያ በተገመተው ምርት መሰረት እንደምርቱ ብዛት እስከ ሶስት ወር በቅድሚያ ሮያሊቲ በመክፈል ይሆናል፡፡

18.<u>**ነባር ፈቃድ ስለማደስ**</u>

1. በአዋጁ ስለፈቃድ እድሳትና ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡የሚከተሉትን በማሟላት የፍቃድ እድሳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡-

ሀ/ ከክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት ደብዳቤ በማቅረብ፤

ለ/ አመልካቶች በፖርታል ምዝገባ ማከናወን አለባቸው፤

ሐ/ ባለፈው የፈቃድ ዘመን የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን፤ ግምታዊ ቀሪ የማዕድን ክምችት እና ዝርዝር የባለሞያ ሪፖርት ሲቀርብ፤

መ/ በማዕድን አዋጁ፤ደንብ በዚህ መመሪያና በፈቃድ ውሉ መሰረት መከናወኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ/ ባለሥልጣኑ ያስፈልጋሉ ብሎ

representation should be issued by the sub-city land development management office;

4. Where farmers wish to operate through a private limited company or partnership or cooperative associations, they shall submit lawful and appropriate evidence from the relevant authorities confirming their establishment/organization under the specified business structures;
5. Any entities organized under farmer associations or other partnership structures shall fulfill all governmental obligations and preconditions necessary to obtain a license;

**16. Registration of License Information**

The Authority shall maintain a register of all applicants who have applied for licenses, including the details of applicants whose applications have been approved or rejected, in accordance with the modern information management system established by the Authority.

**17. <u>Conditions and Time Limits for Issuing Product Lifting License</u>**

1. When the license is terminated due to compelling circumstances before the expiry of its validity period;
2. When the license is revoked and there is not lifted product remaining;
3. When construction minerals accumulated due to various construction activities exist;
4. The product lifting license shall be issued based on the product estimated by professionals and according to the quantity of the

የሚጠይቃቸውን ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሲቀርቡ፤

ረ/ የጥቁር ድንጋይ የማዕድን ፈቃድ የፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ180 /አንድ መቶ ሰማንያ/ ቀናት በፊት የእድሳት ጥያቄ ሲቀርብ፤

ሰ/ ለገረጋንቲ የማዕድን ፈቃድ የፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ90 /ዘጠና/ ቀናት በፊት የእድሳት ጥያቄ ሲቀርብ፤

2. ፈቃዱ ሳይታደስ ከዘገየና ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን እንዲታደስ ከፈቀደ ሳይታደስ ተይዞ የቆየበት አመታት የመሬት ኪራይና የፈቃድ እድሳት እንዲሁም ለዘገየበት ቅጣት ከፍሎ ሊታደስለት ይችላል ፤

3. ቀደም ሲል የቀረበው የአዋጭነት ጥናት ከአምስት አመት በላይ ከሆነና በህጋዊ አማካሪ ከተጠና በነበረው ጥናት ለቀሪው ዘመን ከአምስት አመት ላልበለጠ ጊዜ ጥናቱ ሊያገለግል ይችላል፤

4. የፀደቀ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ከቀረበ በዕድሳት ወቅት የማኔጅመንት ፕላን ማቅረብ ይኖርበታል፤

5. የማዕድን ምርት ወጥቶበት የተጠናቀቀ ቦታ ካለ እና በአግባቡ መልሶ ማልማት የተሰራበት ቦታ መሆኑ ሲራረጋገጥ እንዲሁም በቀጣይ ለማዕድን ማምረት ስራ የማያስፈልግ ቦታ ተቀንሶ ይታደሳል

6. በየሶስት ወሩ ባለፈቃዱ የመልሶ ማልማት አፈጻጻሙን በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

product for a period not exceeding three months upon advance payment of royalty.

**18. Renewal of Existing License**

1. Without prejudice to the provisions of the Proclamation concerning license renewal and the general rights of license holders, license renewal services shall be provided upon fulfillment of the following conditions:

a) Submission of a letter from the Sub-City Environmental Protection Office;
b) Applicants shall complete registration through the portal;
c) Submission of detailed professional reports indicating the major activities carried out during the previous license period, estimated remaining mineral reserves, and related details;
d) Verification that activities have been carried out in accordance with the Mining Proclamation, regulations, this directive, and the license agreement;
e) Submission of additional evidence requested by the Authority as necessary;
f) Submission of black stone mineral license renewal request 90 /thirty/ days before the expiration of the mining license period;
g) Submission of an aggregate mineral license renewal request 90 /thirty/ days before the expiration of the mining license period;

2. If the license renewal is delayed and the licensing Authority permits renewal, the license may be renewed upon payment of

19.<u>ነባር ፈቃድን ማስፋፋት ወይም ማሻሻል</u>

በአዋጁ የፈቃድ ክልሉ የማእድን ክምችቱን ሙሉ በሙሉ የማያካትት ከሆነ ማስፋፊያ የመጠየቅ መብት እንዳለው በተደነገገው መሠረት፡-

1. የማስፋፋት ጥያቄ በማመልከቻ ሲቀርብ፤
2. የማስፋፊያ ቦታው ከነባር ፈቃዱ ኩታገጠም ከሆነ፤
3. የማስፋፋት ጥያቄው አልሚው ከተረከበው ቦታ ከ70 በመቶ በላይ መስራቱ ሲረጋገጥ፤
4. የፈቃዱ ክልል የማዕድናቱን ክምችት በሙሉ የማይዝ ሆኖ ሲገኝ፤
5. አመልካቹ ቀደም ሲል በወሰደው ፈቃድ የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ ከሆነ፤
6. ለአዲስ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የተቀመጡት መረጃዎች ሲሟሉ፤
7. ፈቃዱ የሚፀናበት ዘመን ቀደም ሲል ከተሰጠ የማዕድን ፈቃድ ዘመን የማይበልጥ ሲሆን፤

20.<u>የማምረቻ ማሽን መትከያ ፈቃድ</u>

ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለስራው የሚያስፈልገውን ስፍራ በኪራይ ሊሰጠው የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

1. የድንጋይ መፍጫ ማሽን መትከያና የምርት ማከማቻ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ላለውና በማምረቻ ካባው ውስጥ በቂ ቦታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤
2. ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማዕድን ማምረት ፈቃድ የውል ዘመን መብለጥ የለበትም፤
3. ስለቦታው ለአዲስ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ማግኘት የሚታለፉ ሂደቶችና የሚጠየቁ መረጃዎች

the land rent and license renewal fees for the years during which it remained not renewed;

3. If the previously submitted feasibility study is more than five years old, and if the study prepared by a legally recognized consultant remains valid for the remaining period not exceeding five years, the study may continue to be used;

4. Where an approved Environmental Impact Assessment study has been submitted, an Environmental Management Plan shall be submitted during renewal.

5. Where there is a completed mining production site and it is verified that proper rehabilitation has been carried out, and where the area is no longer required for future mining operations, such area shall be reduced and renewed.

6. The license holder shall have the obligation to submit quarterly reports on overall operational performance in accordance with the prescribed reporting format.

**19.** <u>Expansion or Amendment of Existing License</u>

Pursuant to the provisions of the Proclamation granting the right to request expansion to include other minerals in case the mineral reserve is not fully covered by the existing license boundary:

1. Upon an application for expansion is submitted;
2. Where the expansion area is adjacent to the existing license area;
3. Where it is verified that the

ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

4. የማእድን ማምረቻው ፈቃድ በታደሰበት የጊዜ ልክ የማምረቻ ማሽን ፍቃዱ ሊታደስ ይችላል፤
5. የመንግስት ፕሮጀክት ለሚያለሙ አካላት ፕሮጀክቱን ከሚያሰራው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፤
6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከተቋማቸው የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 21. ፈቃድ ስለማስተላለፍ

1. ፈቃድ የሚያዛውረውና ፈቃድ የሚዛወርለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥያቄያቸውን በማመልከቻ ለፈቃድ ሠጪው መስሪያ ቤት ማቅረብ አለባቸው፤
2. ፈቃድ ከመተላለፉ በፊት ለሚመለከተው የገቢዎች መስሪያ ቤት አመልካቹ ከዕዳ ነጻ ስለመሆኑ ባለስልጣኑ በሚጠይቀው ደብዳቤ መሰረት ምላሽ ማምጣት አለባቸው፤
3. ፈቃድ እንዲተላለፍለት የጠየቀው ድርጅት ህጋዊ ሰነዶች ወይም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የመመስረቻ ጽሁፍ፣የመተዳደርያ ደንብና የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርትፊኬት ያቀርባል፤
4. ፈቃድ ለማዛወር የጠየቀው ድርጅት ከሆነ ውክልና ሕጋዊ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፤
5. ስም ለማዛወር የጠየቀው ባለፈቃድ የማዕድን ማምረት ሥራውን በገባው ውል መሰረት ሥራ ጀምሮ እየሰራ መሆኑን፣ ከልዩ ልዩ ውዝፍ

licensee/developer has operated on more than 70 percent of the allocated area;

4. Where the license area does not fully include the mineral reserves;
5. Where the applicant has fulfilled obligations required under the previously issued license;
6. Where the requirements established for a new mining production license are fulfilled;
7. Provided that the duration of the license shall not exceed the duration of the previously granted mining license;

## 20. Production Machine Installation License

A location outside the license area may be leased for operational purposes only under the fulfillment of the following conditions:

1. A license for installation of stone crushing machinery and product storage may only be granted to a holder of a mining production license where it is verified that there is insufficient space within the production area (quarry area);
2. The validity period of the license shall not exceed the contractual duration of the mining production license;
3. The procedures and information required for obtaining a new mining production license concerning the site shall also be fulfilled;
4. The production machine installation license shall be renewed concurrently with the renewal period of the mining production license;

ክፍያዎች ነፃ መሆኑን የአፈፃጸም ሪፖርት አቅርቦ በባለስልጣኑ መረጋገጥ አለበት፤

6. ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቋሚ እቃዎችን በሙሉ አብረው እንዲዛወሩ ወይም ለሌላ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ ማዞር ወይም ቀረጥ ስለመከፈሉ ክትትል ይደረጋል፤
7. የፈቃድ ስም የሚዞርለት ድርጅት ወይንም ግለሰብ የአዋጭነት ጥናትና የተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ በድጋሚ ማስጠናት አያስፈልገውም፤አስቀድሞ በቀረበው ጥናትና የኢንቫይሮንመንታል ማኔጅመንት ፕላን መሰረት እንዲቀጥል ይደረጋል፤
8. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ድንጋጌ ቢኖርም በቀጣይ ለሚጠይቃቸው አገልግሎቶች የራሱን የአዋጭነት ጥናት ማቅረብ ይኖርበታል፤ እንዲሁም የማኔጅመንት ፕላን እንዲያቀርብ ይደረጋል፤
9. ቀደም ሲል ለመልሶ ማልማት የተያዘውን ገንዘብ ስም የዞረለት ግለስብ ወይም ድርጅት ገቢ ማድረጉ ሲረጋገጥ ቀድሞ የተያዘው እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

**22.<u>የፈቃድ ስም ማስተላለፍ የሚቻልባቸው ምክንያቶች</u>**

1. በውርስ፣
2. በሽያጭ ወይም በመዳረግ፣
3. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊተላለፉ ይችላል፡፡

**23.<u>የፈቃድ ስም ማስተላለፍ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች</u>**

1. ድርጅቱ በኪሳራ ላይ ያለ እና ዕዳ

5. Entities implementing government projects shall submit a support letter from the project's employer;
6. Government development enterprises shall submit a support letter from their respective institutions;

**21. <u>Transfer of License</u>**

1. The person or organization transferring the license and the transferee shall submit their request to the licensing office through an application;
2. Before the license is transferred, the transferee shall submit a response that prove the applicant is free from debt in accordance with the authority's enquiry letter;
3. The organization requesting the transfer of the license shall submit legal documents including the business registration certificate, the organization's general manager, memorandum of association, articles of association, and taxpayer registration certificate;
4. Where the applicant requesting the license transfer is an organization, recognized power of attorney and legal documents shall be submitted to the Authority from the relevant body;
5. The license holder requesting name transfer shall submit a performance report proving that mining production activities are being conducted according to the agreement, and confirming that the holder is free from various outstanding payments, subject to verification by the Authority;
6. Monitoring shall be conducted to ensure that all duty-free imported

ኖሮበት ያልከፈለ ከሆነ፤

2. እየፈረሰ ላለ ድርጅት
3. በማጭበርበር ወይም የተሳሳተ ማስረጃ በማቅረብ ለማጭበርበር ከሞከረ፤
4. ሕጋዊ ሰውነት ላላገኘ ማህበር ወይም ድርጅት፡፡

24.<u>የፈቃድ ስም ለውጥ</u>

አመልካቹ ማህበር ከሆነ በቅድሚያ ከአደራጃቸው አካል እና ከገቢዎች ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎች ከሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ስም የለወጠበትን ተገቢውን መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤ አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ በቀድሞ ፈቃድ ላይ ችግር የማይፈጥር ከሆነ በጥያቄው መሰረት የስም ማስተካከያ ይደረጋል፤

25.<u>የድጋፍ ደብዳቤ ስለማግኘት</u>

ማንኛውም የታደሰ የማዕድን ፈቃድ ያለው ሰው ለተለያዩ መስሪያ ቤቶች የድጋፍ ደብዳቤ ለመፃፍ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

1. አምርቶ ለሸጠው የማዕድን ምርት የሮያሊቲ ክፍያ ከፍሎ ማጠናቀቅ፤
2. በማምረት ስራ ላይ ስለመሆኑ ያለውን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማቅረብ፣
3. የማዕድን አዋጅ፤ መመሪያና የፈቃድ ውል ግዴታዎችን ማክበር፤

26.<u>መንግስታዊ ፕሮጀክት ያላቸውና የመንግስት ልማት ድርጅቶች</u>

1. የማምረት ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት ይኖባቸዋል፣
2. በየወሩ ያመረቱትን ምርት ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ወር በገባ የመጀመሪያው ሳምንት ሰኞ ማቅረብ

permanent goods are transferred together with the license, transferred to another duty-free beneficiary, or that duties have been duly paid;

7. The organization or individual to whom the license name is transferred shall not be required to conduct a new feasibility study or Environmental Impact Assessment study; operations shall continue based on the previously submitted study and Environmental Management Plan;

8. Notwithstanding Sub-Article (7) of this Article, the transferee shall submit its own feasibility study for future requested services and shall also submit a Management Plan;

9. Upon verification that the transferee individual or organization has deposited the previously reserved rehabilitation fund, the earlier withheld amount shall be released.

**22.** <u>Grounds for Transfer of License Name</u>

1. By inheritance;
2. By sale or assignment;
3. By court order;

**23.** <u>Conditions Under Which Transfer of License Name is Not Allowed</u>

1. Where the organization is bankrupt and has unpaid debts
2. For an organization undergoing dissolution;
3. Where an attempt was made on fraudulent acts or submission of false evidence;
4. For an association or organization that lacks legal personality.

**24.** <u>Change of License Name</u>

ይኖርባቸዋል፤

3. የመንግስት ልማት የሚሰሩ የግል ድርጅቶችን በተመለከተ የድጋፍ ደብዳቤ ከሚያሰራው ተቋም ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፤እንደማንኛውም አልሚ ካመረቱት ላይ በወቅቱ ዋጋ መሰረት ለመንግስት ሮያለቲ ይከፍላሉ፤
4. የመሰረተ ልማት ስራው ከተጠናቀቀ ቦታውን ከሰጠው አካል ስምምነት በማምጣት ለአዲስ የማዕድን ፈቃድ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ፈቃዱን መቀጠል ይችላል፤
5. ለመንግስታዊ ድርጅት የሚስጥ ፈቃድ ስራውን እያከናወነ ማህበራዊ ልማቶችንና ጎን ለጎን የመልሶ ማልማት ግዴታ ማከናወን አለበት፤

27.<u>ፈቃድ የሚሰረዝባቸው ምክንያቶች</u>

በደንቡ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. አልሚው ፈቃድ እንዲሰረዝለት በማመልከቻ ሲጠይቅ፤
2. ቦታው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ለሌላ ልማት ሲፈለግ፤
3. ቀሪው ቦታ በቀጣይ የማያሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ፤በባለስልጣኑ የተናጠል ፍላጎት በደብዳቤ አሳውቆ ሲሰርዘው፤
4. የመሬት ኪራይ ውል ዘመኑ ሲጠናቀቅና የውል ማራዘሚያ ስምምነት ማቅረብ ካልተቻለ፤
5. አልሚው ከውል ውጭ በሆነ መንገድ ተደጋጋሚ ሕገወጥ ድርጊት ከፈፀመ፤
6. በአዋጁ፣ ደንብና በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱ ግዴታዎችን ካላከበረ፤

If the applicant is an association, the relevant information regarding the name transfer must be submitted in advance by the establishing institution, the Revenue Authority, and any other competent legal bodies. If the applicant is an individual and there are no issues with the previous license, the name change shall be processed as per the request.

**25.** <u>Obtaining Support Letter</u>

The following preconditions shall be fulfilled for issuance of support letters to various offices; accordingly, any holder of a renewed mining license shall:

1. Complete payment of royalty fees for mined and sold mineral products;
2. Submit operational activity reports proving that they are engaged in mining activities;
3. Comply with obligations stipulated under the Mining Proclamation, directives, and license agreement.

**26.** <u>Government Projects and Public Development Enterprises</u>

1. They shall obtain a production license from the Authority;
2. They shall submit monthly production reports to the Authority within the first week of the following month, on Monday;
3. Private enterprises engaged in government development projects shall submit a support letter from the project employer or relevant institution to the Authority. In addition, like other developers, they shall pay royalty to the government based on the prevailing market price of their production;

7. ማዕድኑ ካለቀ ፈቃዱ ተሰርዞ ለባለይዞታው አግባብ ባለው አካል እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

28.**<u>ስለጥፋቶችና የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>**

ማንኛውም ሰው በወንጀል በፍትሐብሔር ተጠያቂ ሊደረግ የሚችል መሆኑ እንደ ተጠበቁ ሆነው በአዋጁ እና ደንቡ ላይ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

29.**<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግደታ አለበት፡፡

30.**<u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች</u>**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ባለሥልኑ ያወጣው መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

31.**<u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፤ ሰኔ፣ 2018 ዓ.ም**

**ዶ/ር እሸቱ ለማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን**
**ዋና ሥራ አስኪያጅ**

4. Upon completion of infrastructure works, they may continue their operations by obtaining agreement from the land - providing body and fulfilling the conditions set for a new mining license;
5. For license granted to governmental organization, the license holders shall, in the course of their operations, also undertake social developmental works and environmental rehabilitation activities alongside their tasks.

**27. <u>Grounds for License Cancellation</u>**

Without prejudice to the provisions of the Regulation:

1. When the developer requests cancellation through application;
2. When the land is fully or partially required by the government for other development purposes;
3. When the remaining land is confirmed to be not suitable for continued operation and the Authority notifies cancellation by letter at its discretion;
4. When the land lease contract period expires and renewal agreement is not submitted;
5. When the developer repeatedly commits unlawful acts outside the contract;
6. When obligations set out in the Proclamation, Regulation, and this Directive are not complied with;
7. When the mineral resource is exhausted, the license shall be cancelled and the land returned to the rightful holder through the appropriate authority.

**28. <u>Offences and Measures to be Taken</u>**

Without prejudice to criminal and civil liability, any person shall be held accountable in accordance with the provisions of the Proclamation and Regulation.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 29. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Directive.

### 30. Non-Applicable Directives

Any directive or customary practice issued by the Authority that contradicts the provisions of this Directive shall not be applicable to matters covered under this Directive.

### 31. Effective Date of the Directive

This Directive shall enter into force on the date it is registered by the Ministry of Justice and published on the Authority's website.

**Addis Ababa; July,2026**

**Eshetu Lemma (phd)**
**Addis Ababa City Environmental Protection Authority**
**General Manager**